המינהל הפדגוגי – אגף שפ"י - הורים ומשפחה והאגף לקליטת תלמידים עולים ותושבים חוזרים

የተከበራችሁ ወላጆች

ዘመቻ "ብረት ሠይፍ" የተጀመረበትን ቀንና ዓመት አስመልክቶ በየትምህርት ተቋማቱ የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባሮች ይደረጋሉ። የትምህርታዊ ተግባሮች ስፋትና ጥልቀት እንደ ተማሪዎች እድሜ፣ ችሎታና ብቃት በትምህርት ቤቶች የሚወሰኑ ይሆናሉ። ዓመቱን ሙሉ በተለይ ደግሞ የመታሰቢያው ቀን መዳረሻ ሰሞን በትምህርት ተቋማት የሚያገለግሉ ባለሙያዎች ስለጦርነቱ ለተማሪዎቻቸው ስለሚሰጡአቸው ትምህርታዊ ተግባራት በእውቀት ማገዝና ትምህርቱ ለተማሪዎችም ለመምህራኑም የሚመጥን እንዲሆን መርዳት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ በሞት ያጣችሁት ወይም የቆሰለ የቤተሰብ ዓባል ሊኖር ይችላል፤ በሃማስ ከተጠለፉት ሰዎች ጋር ዝምድና ወይም እውቂያ ሊኖራችሁ ይችላል፤ እንዲሁም ከቆሰሉት ወይም ቤታቸውን ጥለው ከተሰደዱት፣ ወይም ግዳጅ ተቀብሎ ግንባር ላይ የሚገኝ ዘመድ ወይም በየትኛውም የደህንነት ክፍል የቆመ ዘመድ ይኖራችኋል፤ ወይም በእናንተና በልጆቻችሁ ሕይወት ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ሁኔታ ይኖራል።
እንደ ወላጅ ከተለያዩ ተግዳሮቶች ጋር እየተጋፈጣችሁ ትገኛላችሁ። ችግሩ ቀላል አይደለም። ምናልባትም ጥያቄዎች በራሳችሁ ተውጠንጥነው ይሆናል፡- ልጄ ምን ያውቃል፣ ምን ያህልስ ይረዳል? ምን ላብራራለት? ከተለያዩ ወሬዎች እንዴት ልጠብቀው፣ ይህስ ይቻላል ወይ? ጥንካሬና ደህንነት እንዴት ላሳየው እችላለሁ፣ ከዚህ ጋር አብሮስ ማሰብም መስጋትም እንደሚቻል እንዴት ላስገነዝበው እችላለሁ? እና ደግሞ በውስጤ ለልጄ ስል ጉልበትና ጥንካሬ እንዴት አገኛለሁ?

በዚህ ጊዜ ከልጆቻችሁ ጎን ለመቆም የሚረዳችሁ ምን ሊሆን ይችላል?

ከልጆቻችሁ ጋር ተወያዩ፡- ምን እንዳገኛቸው፣ ምን እንደሚሰማቸው፣ ምን እንደሚያስቡ መርምሩ እና ከጎናቸው እንደሆናችሁ አረጋግጡላቸው።

መልሶቻችሁ ተስፋን መመኪያነትን እና ደህንነትን ያዘሉ ይሁኑ፡- ልጆቻችሁ ታላላቆች እንደሚያስቡላቸውና እንደሚጠብቋቸው አረጋግጡላቸው። "እኛን የሚጠብቅ አለን" በማለት እናንተ ቤተሰቦች በአንድ ላይ ጠንካሮች እንደሆናችሁና እርስ በእርሳአችሁ እንደምትጠባበቁ ንገሯቸው።

ለልጆቻችሁ ቀጥተኛና ትክክለኛ መልስ ስጡ፤ እውነተኛና ለእድሜአቸው የሚመጥኑ ይሁኑ። ስትመልሱ ብዙ ትንተና ውስጥ መግባት የለባችሁም።

ርህራሄና ሆደሰፊነት ይኑራችሁ፡- ለሁኔታዎች የልጆች ባሕሪያዊ ግብረመልስ የተለያየ ነው፤ (ጠባጫሪነት፣ አልቃሻነት፣ ድባቴና ሌሎችም)፣ ትግስት ይኑራችሁ፣ እየደባበሳችሁ ሙቀት ስጡአቸው፣ ብዙ እያጫወታችሁ በአንዳንድ ሥራዎች እንዲሳተፉ አበረታቱአቸው። የተራዘመ የባሕርይ ለውጥ በሚያሳዩ ጊዜ ከትምህርት ባለሙያዎች ጋር መመካከር ያስፈልጋል።

ከልጆቻችሁ ጋር በመሆን እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዴት እንደምትረዱ ዘይዱ፤ (ለምሳሌ ስ ዕ ል በመሳል ለወታደር ቤተሰብ መላክ፣ ለጎረቤታችሁ ኬክ መስጠት፣ ቅርብ ዘመዶቻቸው ወደ ግንባር የሄዱባቸውን የጎረቤቶቻችሁ ልጆች እራት መጋበዝ እና ሌሎችም)።

በየቀኑ፣ ጊዜው እንደበቃችሁ፣ ፈታ የሚያደርግ የቤተሰብ የጋራ ጊዜ ይኑራችሁ፡- ይህም ጥሩ የመቀራረብ መንፈስና የአለኝታነት ስሜት እንዲፈጠር ያደርጋል።

ለልጆቻችሁ እድሜ የማይመጥኑ ዜናዎችና ምስሎችን ከማሳየት ታቀቡ፡- ልጆች የማያዩና የማይሰሙ መስለው ይገነዘባሉና በቴሌቪዥን በሚተላለፉ ነገሮች ላይ ትኩረትና ጥንቃቄ አድርጉ።

የተከበራችሁ ወላጆች፣ ራሳችሁን ጠብቁ። እንዴት እንደምትቋቋሙ ለሌሎች አሳትፉ፤ አንዳንድ ድርጊቶች እናንተን ሊያበረታቱና ተስፋ እንዲኖራችሁ ሊረዱአችሁ የሚችሉትን ጊዜ በመስጠት አድርጓቸው። አስታውሱ ብቻችሁን አይደላችሁም! በትምህርት ቤት የትምህርት ባለሙያዎች ከእናንተ ጋርና ከጎናችሁ ናቸው።

ስሜታችሁን ለማካፈልና ለመመካከር ወደ እኛ ደውሉ፣ እኛ ሁልጊዜም ከእናንተ ጋር ነን። አስፈላጊ ሲሆንም ለትምህርት ሚኒስትር የምክር እርዳታ መስጫ በስልክ ቁጥር *6552 ቅጥያ 5 በመደወል የምክር እርዳታ ማግኘት ይቻላል።

መልካም ጊዜ እንዲመጣላችሁ እንመኛለን